2015/02/06

# ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ

ባለፈው ቅዳሜ ወደ  አንድ ወዳጄ ቤት ለዕንግድነት ሄጄ የራሳችንን ወሬ ቆጥበን ወያኔ አፓና ካናል በሚባል የቴሌቪዥን መስኮት የሚያስተላልፈውን  እንድናይ ተወስኖ የሁላችንም ቀልብ ፕሮግራሙ ላይ አረፈ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የወያኔ የሳምንቱ ዕንግዶች ብቅ አሉ:: ኮሜዲያኑ አቶ ታደሰ ኮስትሬና ወያላው ኢንቨስተር ለእይታ በቁ:: አቶ ታደሰ ኮስትሬ ካለፈው ቅዳሜ ሳምንት በፊት ቀርበው ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ የሰጡትን አስተያየት በ ethiopatriots.com ላይ ተለጥፎ አውድዮውን ስላደመጥኩ ዛሬ ደሞ ምን ሊሉ ነው ብየ በጥሞና ቃለምልልሱን ተከታተልኩ:: ለዕንግድነት የሄድኩባቸውም ወዳጆች እንደኔው አቶ ታደሰ  በዚሁ በስቶክሆልም ቀደም ሲል ሲያደርጓቸው በነበረው የተቃዋሚነት ትግል ስለምናውቃቸው በዚህ ሁኔታ ሰተት ብለው ገብተው ባለሟል ሆነው መታየታቸውን ሰቀጠጠን:: አይ የሰው ልጅ ከንቱ ነው አልን:: ባለሟሉ የውይይቱ ደቂቃዎች እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ግን ጭቃ ጅራፋቸውን መርጨት ጀመሩ:: የዚያኑ ያህል ማዳመጥ ይሰቀጥጥ ነበር:: በቁም ሞት ማለት እንደዚህ ነው ለካ አልኩ:: አምላኬ ዕድሜየን ቀጥልልኝ ማለት እንደዚህ ወደአለው ውርደት የሚያደርስ ከሆነ እግዚአብሄርም አንደበቴን ጠብቅልኝ፣ ማንነቴን አታስተኝ ማለት እንደሚመረጥ ከአቶ ታደሰ ኮስትሬ በኋላ ወሰንኩ::

ከሁሉም በላይ የደነቀኝን ላካፍላችሁ:: አቶ ታደሰ ኮስትሬ ተቃዋሚዎችን ሲከሱ እንዲህ አሉ አውቃቸዋለው ጥቂቶች ናቸው አሉ:: ቁጥሩን አልተናገሩም:: የቁጥር ሰውም አይደሉምና:: የሕግ ምሩቅ ነኝ ብለውናል:: የሚገርመው ግን በመድኅን፣ በመድኅን/ ኢደፓ፣ በትንሣዔ ሬድዮ፣ በግንቦት 7 እያሉ ሲያገላብጡ በነበረበት ዘመን (የቅርብ ትዝታ ነው) እሳቸውና አንድ ጓደኛቸው ብቻ ነበሩ:: በድርጅት ስም ታቅፈው፣ ሁለት ብቻ ሆነው አለተለዋዋጭ አባልና አለኮሚቴ ተጠሪ የነበሩት ዛሬ ምነው ስለቁጥር ማነስ ማውራት ፈለጉ ? እሳቸው ያለፉበት ታሪክ ተዘነጋቸው እንዴ ? ወይንስ ድሮም ትግል ውስጥ አልነበርኩም ነው የሚሉን ? አይ ዕድሜ፥ ከአረጁ አይበጁ:: እነዚህ ትንሽ ናቸው የሚሏቸው ሰዎች ግን ለሕዝብ መብት ይከራከራሉ:: በሰውም ሆነ በእግዚአብሄር ፊት የሚያስከብር ሥራ ይሰራሉ:: እርስዎ ሁለት ሆኖ መስራት መቻሉን ተረድተው ዘጥ ዘጥ ሲሉ ሌላው ታድያ ወጣት ጐረምሳ  ሁለቱ ሽማግሌዎች አራት ሆነው ሊበራከቱ አይችሉም ብለው ይሆን ? አቶ ታደሰ ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ሆነብዎት፣ ዞረው ዞረው ቁጥር ምን ያህል መሆኑን ወደ አልተረዱበት ዘመን ተመለሱ: ያ የቀልድ ዘመን አልፏል:: ዛሬ ሌላ ዘመን ላይ ነን!! ባንዳው ተለይቷል::

ከአቶ ታደሰ ኮስትሬ በፊት የወየኑ በአጠገባቸው አሉ:: ለምን ነባሮች ወያኔዎች እያሉ አዲስ ባለሟል ወያኔ ቡድን ሾመ የሚለው ከአንድ ነገር ጋር ያያይዘዋል:: አቶ ታደሰ በቀደመ ታሪካቸው ኮሜድያን፣ ኦርኬስትራ፣ አስተዋዋቂ ናቸው:: ለእሳቸው ሳይሆን ለሙያው አክብሮት አለኝ:: በተፈጥሮዋቸው መድረክ ላይ ልታይን ይወዳሉ:: ባለቀ ሰዓት ነፍሳቸው ከአንድ ዛፍ ወደሌላ መንጠላጠል መፈለጓ በምድርም በሰማይም ርግማኑን ልብስ ላድርገው ብለው ቆርጠዋል::

መቼም ጅብ ከማያቁበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ እንዳለው ሆነና በስደቱ ዓለም ከአቶ ታደሰ የሌላቸውን አለኝ አሉ:: ለዛውም የሕግ ምሩቅ መሆናቸውን ነገሩን:: እንኳን የምጣኔ  ሐብት ምሩቅ ነኝ አላሉን፣ በቁጥር ግምትዎ እንሚገትዎት ነበር:: ዛሬ ግን የሕግ ዲግሪ በእጅዎ ስለሆነ የምንነጋገረውን እንድናውቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥተወናል:: እንዳውም አንድ ነገር ልጠይቀዎትና የትኛው ዩንቨርሲቲ ገብተው ነበር ? የምርዎትን ነው ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ያሉት? የዩንቨርሲቲው ግቢ በየት በኩል

እንደሆነ ያውቁታል ወይ? አስተማሪዎችዎስ ከነበሩት ውስጥ ማንን ይጠራሉ? ምን ያድርጉ እርስዎ ወደ ወያኔ መደባለቅ እኮ ዲግሪ እያስጠየቀ መጥቷል። አርቲስት፣ አዝማሪ፣ ኮሜድያን ወያናዊ መሆን በቂ አይደለም፣ ዘመኑ ተለውጦ የወያኔ ሚንስትሮች ሁሉ ከውጭ አገር ዲግሪውን ሸምተውታል። ለእርስዎስ ይህ እንዴት ይነስዎት? ከወያኔ ጋር ሲደባለቁ አንሰው ተገኙ እንዴ? ባለ ዲግሪ ነኝ አሉ! አይ ቅሌት!!

ሰሞኑን አዲስ አበባ የተፈፀመውን ዘግናኝ ቲያትርና አቶ ታደሰ ኩስትሬን ነብይነት ገጥሞላቸው ሲገኝ ከተደነቁት አንዱ ነኝ። አቶ ታደሰ  በአቶ መለስ መሞት እርግጠኛ አይደሉም። ከፍተኛ ጥርጣሬ አላቸው። እሳቸው እንዳሉን አቶ መለስ አልሞቱም ብየ ሃዘኔን ገልጫለው እወቁልኝ ብለውናል። ይህ ብቸኛው የአቶ ታደሰ ኩስትሬ ትንቢት ደርሶላቸው እንደነበር ከአዲስ አበባ የተላለፈው ዜና ነገረን። በሃገራችን ድንቅ ነው ተብሎ የሚነገርለት የሕዝብ መጓጓዢ የባቡር መስመር የመዘርጋት ግንባታ  አንዱ ሲሆን፣ ይህንኑ ተሰርቷል የተባለውን የታቀደለትን ሙከራ በስፍራው ተገኝቶ የመጀመሪያ መንገደኛ ለመሆን አሉ የተባሉ የወያኔ ባለስልጣናት በተሰበሰቡበት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ወደ ባቡሩ እየገቡ ነው ሲል እንደነበር የቴሌቪዥን ዘጋቢው ዲስኩር ሲያረግ ተደምጧል። አደራ አቶ ታደሰ ኩስትሬ እርስዎም በተሰጥዎት ቲቪ ይድገሙልን። እኔን የገረመኝ ጋዜጠኛው በአካባቢው ላልነበሩት ሲናገር አቶ መለስና ሚኒስትሮች በባቡር ውስጥ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል አለ የወያኔ ቀልጣፋ ካድሬ። አቶ ታደሰ ከሚሉን ጋር ገጠመላቸው። አቶ ታደሰ አቶ መለስ አለ የሚሉትን ጋዜጠኛው አረጋገጠ። ሟቹ መለስ የመረቁትን ባቡር አቶ ታደሰ ኩስትሬ አልሞትክም ብያለው ያሉትን ሄደው ከመለስ ጐን ቆመው ለመመረቅ እድሉን አለማግኘታቸው በመኖርና ባለመኖር መካከል ያለውን ይረዱ ነበር ብየ እገምታለው።

በውጭ አገር ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ መካከል አብዛኛው ሲያውደለድል የኖረው ብዙ ነው። በ social welfare ድጐማ ሰው መስሎ ለብሶ ይታይ የነበረው በጡረታው ዕድሜ ማጣፊያው ያጥርቦታል። በተለይም የጡረታ አበል ስለሚያንስ ሱፍ ለብሶ ቀለም ተቀብቶ በአደባባይ ለመታየት ወጪው ብዙ ነው። አቶ ታደሰ ክህደቱ ድጐማ ያስፈልጋቸዋል። ለዚህ ነው ከወያኔ በላይ ወያኔ ሆኛለው የሚሉን። አቶ ታደሰ የተጫኑትን ለመዘርገፍ የአንድ ሰዓት ፕሮግራም አይበቃቸውም። ወያኔ የሁለት ሰዓት ስርጭት መጀመር  ይኖርበታል፣ ወይንም ከትግራይ ነፃ አውጪ ማኅበሩ ቲቪ ይዋሱላቸው። በእርሳቸው አበረታችነት የሚኰለኰለው እንግዳ ቁጥሩ እንደሚጨምር ግልፅ ነው። ባለፉት ሳምንታቶች ንግግራቸው የአምባሳደርነትን ቦታ የያዙ ይመስላል። ማንነታቸውን ለወያኔ ማደሪያ ስላደረጉ በገፅታቸው ላይ ግን ውርደት፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት ይታይባቸዋል። ገና በወያኔ ቤት አልተደላደሉም።

ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ወደራሴ ሕይወት ተመልሼ አንተ ፈጣሪ ምን ልለምንህ? ዕድሜ ወይንስ ጨዋነት ወይንስ ሁለቱንም አልኩ? የቁም ሞት መጥፎ ነውና? ግራና ቀኙን ያስተዛዝበናልና? ፈጣሪን እንደበቴን ጠብቅልኝ፣ ከሐጢያት ነፃ መውጣት የምትፈልግ ነፍስ ዋጋዋን በሚገባ ታውቃለች። በሐጢያት ነፃ መውጣቷ በሥጋ በአካባቢዋና በአጋንንት ከመዋረድ እጅግ የሚበልጥና የሚከበር እንደሆነም ትጠነቀቃለች።

እግዚአብሄር ኖሬም ሆነ ቆሜ ከተወቃሽነት ጠብቀኝ። ስብዕናን መጣል የህሊና መራቆት ነው። ሰው በተፈጥሮ ያገኘውን ማንነት የሚያሳጣው ለጥቅም ሲገዛ ነው። በመሆኑም በጥቅም ጉጉት ሲዋዥቅ የነበረ ሰው አወዳደቁ አያምርም። አቶ ታደሰ ኩስትሬ ለጥቅም መገዛትን ወደው  በመቀበላቸው በጥቅም ባርነት ቀንበር ውስጥ ሰለገቡ ከስንት አመት በኋላ አዲስ ሰው ሆነው ብቅ አሉ። የተሸሸገውን ማንነታቸውን በጣራው ዕድሜያቸው ይፋ አደረጉት። አይ መካሪ ማጣት እናንተ አቶ ታደሰን ልካችሁ በአደባባይ እንዲዋረዱ ያረጋቹሁ ሰዎች ነፍሳችሁ አይማርም። ከሐጢአቱ የእናንተም ነው። ከወያኔ ጋር ያላችሁ ጥቅም ምክንያት ጭልጥ ብላችሁ ተኝታችሁ እኝህን የጡረታ አበል ያነሳቸውን መላካችሁ

እጅጉን በምድርም በሰማይም እርግማን እንደሚደርስባቹህ እወቁት። አቶ ታደሰ ላይመለሱ ጭልጥ ብለው ገብተዋል። በድጋሚ ልበለውና ከኮሜድያንነት ወደ ትንቢተኛነት የተሸጋገሩት አቶ ታደሰ ኰስትሬ በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ አጥተዋል። ፈጣሪየ መጨረሻየን አሳምርልኝ። ለአቶ ታደሰ እንፀልይ።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ  ፀረ ዕውቀት በመሆን እንደዋና የእውቀት መረጃ አድርጐ የሚያየው የፈጠራን ወሬ ነው። ማንበብ፣ ማገናዘብ፣የማወቅ ጉጉት ሳይሆን በውስጡ ያለው የመንደር ወሬ መቀለብን ይመርጣል። ከሰው ተርታ የወጣው ብዙ ነው። ስለዚህ አገራችን ሰው አጥታለች። የእኛን ህብረተሰብን የምናይበትን መነፅር የለገሰንን ፈላስፋ ንግግር ላንሳና ፁሑፌን ላጠናቅቅ፣ ፈላስፋው የግሪክ ተወላጅ ነው። ይህ ሰው ከክርስቶስ መወለድ ከ400 ዓመቶች በፊት በሕይወት ዘመኑ የተናገራቸው ዛሬም የሰው ዘር የሆነ ሁሉ አስተሳሰቡን ይጠቅሰዋል። ግሪካዊ ፈላስፋ ዲያጀነስ (Diogenes) ይባላል። ሐብት ባላቸውና፣ በሌላቸው መካከል፣ ስብዕና ባላቸውና በሌላቸው መካከል ያለውን የሰው ልጅ ክፋት እያየ ተማርሮ ከእንስሳ ጋር መዋል ጀመረ። ውሻዎችን አፈቀረ ከውሾች ጋር መኖርን ተላመደና በከተማው ከውሾች ጋር ይንከራተታል። የሚያውቁት ሰዎች ሁሉ ምንነካህ? ምን እየፈለክ ነው ብለው ጠየቁት አንድ ሰው የሆነ እየፈለኩ ነው ብሎ መለሰላቸው። ይህ ሁሉ ሰው አይደለም እንዴ አሉት?  አይ ብቻ አንድ ሰው ላግኝ ምናልባትም ፈልጌ አገኘው ይሆናል አለ። እግርም አይኑረው፣ ዱዳም ይሁን፣ ጅልም ይሁን ብቻ ግን አንድ ሰው አለ። በመቀጠልም ለክብር ዋጋ የሚሰጥ ፣ ህሊና ያለው፣ ስብዕና ትሁትና በጐ አሳቢ፣ የተቆጠበ፣ ለሰው ልጅ በጐ ነገር የሚያስብ፣ ከተበደለ ጋር የሚወግን ብሎ መለሰላቸው። ከዚያን ዘመን ጀምሮ ይቺ ከንቱ ዓለም ሰው ፍለጋ ላይ ነች። የግሪኩ ፈላስፋ ከዚያን ዘመን በኋላ በዜና መለስ ሰሞኑን እንደተነሳው ሳይሆን በእውነተኛ የሰው ልጅ ባህሪው ቢመለስ የሚያገኘው ብዙ ታደሰ ኰስትሬዎችን ነው። ይህ ፈላስፋ ይህን አስከፊ ዓለምና የሰፈሩበትን ክፉ ሰዎች ከማየት ተገላግሏል። የአገሬ ሰዎች የዘመናችን ባንዳዎች ይህ ፈላስፋ አይገልፃቸውም ብላችሁ ነው።   *ይቀጥላል*

ከስቶክሆልም  ታዛቢ